# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 1 ቁጥር 52 ነሃሴ 24 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

# አዲስ አበባ

## ሁሉን ጠቅልላ የያዘችው አጨቃጫቂ ከተማ

(በአማኑይሁን ሲ. )



# አዲስ አበባ

## ሁሉን ጠቅልላ የያዘችው አጨቃጫቂ ከተማ

## አማራጭ መፍትሄ

በአማንይሁን ሲ.

### አዲስ አበባ፤ ስያሜ፣ ምስረታና ዕድገት (ታሪካዊ ዕይታ)

በዘመናዊት ኢትዮጵያ የከተሞች ታሪክ ውስጥ የአዲስ አበባን ያህል የበረከተ ሚና ያላት፣ ተጽኖዋ የገዘፈና ድንበር የተሻገረ፣ እንደዚሁም ዓለምዓቀፍ ገጽታን የተላበሰችከተማ የለም።ይሁን እንጂ ይች ታሪካዊ ከተማ ከምስረታዋ ጀምሮ ስታጨቃጭቅና የባለቤትነት ጥያቄ በተደጋጋሚ እየተነሳባት ስታወዛግብ የከረመች መዲና ናት። አዲስ አበባ የተመሰረተችው የሸዋው ንጉሥበኋላም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የሆኑት ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ በ1879 መናገሻቸውን ከአንኮበር ወደ እንጦጦ በማዞራቸው ነው። የእንጦጦ ቅዝቃዜ አስቸጋሪ የነበረ በመሆኑ ባለቤታቸው እተጌ ጣይቱ ንጉሱ ለዘመቻ እንደሄዱ ከእንጦጦ ወደ ታች ዝቅ ብለው ፍል ውሐ አካባቢ ሰፍረው ጠበቋቸው። ምንም እንኳን የእንጦጦ ተራራ ለወታደራዊ ተልዕኮ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታው ከፍተኛ የነበረ ቢሆንም፤ የፍል ውሐ አካባቢ የነበረው የተሻለ አየር ንብረትና አስተማማኝ የውኃ አቅርቦት የንግስቲቱን ቀልብ ስቦት ነበር።

ይህች ስያሜዋን በእተጌ ጣይቱ አማካኝነት ካደመቋት የአደይ አበባዎች የቀሰመችው ከተማ ከአድዋ ጦርነት በኋላ ይበልጥ እየሰፋችና እየዘመነች መጣች።በበርካታ የግንባታ ሥራዎቿም የአውሮፓ፣ የኤሲያና የመካከለኛው ምስራቅ ባለሙያዎችን በማሳተፍ በከፍተኛ ፍጥነት እየሰፋችና ዘመናዊነትን እየተላበሰች መጣች።

አፄ ሚኒሊክ የዘመናዊ ሀገረ-መንግሥት አስፈላጊነትን በጣም ይረዱ ስለነበር ኢትዮጵያን ከአውሮጳቴክኖሎጂ ጋር ማስተዋወቅን ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ይሠሩ ነበር። በመሆኑም መናገሻቸውን በባለቤታቸው ምርጫ አዲስ አበባ ላይ ካደረጉ በኋላ ሙሉ ትኩረታቸው መንግሥታቸውን ማጠናከርና ማዘመን ላይ ነበር።

ንጉሡበ1884 ጀምሮ የመንግሥትን የገንዘብ አቅም በማሳደግ ኢትዮጵያን ለማዘመንና የልማት አውታሮችን ለማስፋፋት የሚያስፈልገውን ፋይናንስ ለመሰብሰብ የዘመናዊ የግብር ሥርዓትን አስፈላጊነት በመረዳት በአዲስ አበባ የግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት አቋቋሙ።በዛው ዓመት የታላቁ የሚኒሊክ ቤተመንግሥት በመባል የሚታወቀውን ቤተ-መንግስታቸውን ማሳነጽ ጀመሩ።ከሁለት ዓመት በኋላ ደግሞ ማሪያ ትሬዛ የተባለውን የኦስትሪያ የመገበያያ ገንዘብ ሥራ ላይ በማዋል ንግድ እንዲዘምን ፈር ቀደዱ። በመቀጠልም የፖስታ አገልግሎትንበከተማው ሥራ አስጀመሩ።

በዚህ ጥረታቸው ላይ እያሉ ገና የንጉሠነገሥትነት አክሊላቸውን ሳይደፉ አሰብ ላይ እግሩን ያሳረፈው የጣሊያን ወራሪ ቀስ በቀስ ድንበር እየገፋ ኢትዮጵያን የመውረር ፍላጎቱን በይፋ ያሳይ ጀመር። በመሆኑም ይህን የሀገር አንድነት የሚፈታተን የቅኝ ገዢ ለመመከት ዝግጅት እያደረጉ በሌላ በኩል ደግሞ ሀገራቸውን የማልማት ሥራቸውን አጧጡፈው ቀጠሉ።

ንጉሡ በአንድ በኩል ሀገረ-መንግሥት የማጽናትሥራን እያጠናከሩ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ወራሪን ለመመከት ዝግጅት ላይ እያሉ ኢትዮጵያ በዘመኗ አይታ የማታውቀው እጅግ የበረታ ድርቅና ረሃብ ተጋረጠባት። ክፉ ቀን በተባለውና ለአራት ዓመታት ብርቱ ክንዱን ባሳረፈባት ድርቅ ምክንያት ኢትዮጵያ ካሏት የቀንድ ከብት ኃብት ከግማሽ በላይ ገብራ፤ ከአንድ ሚሊዮን የሚበልጡ ልጆቿን በርሃብ አለንጋ አስቀጥፋ ክፉውን ቀን አለፈችው። ንጉሠ ነገሥቱም ባንድ በኩል ለአይቀሬው ጦርነት እየተዘጋጁ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ ከርሃቡ እንዲያገግምና የሀገረ-መንግሥታቸውን የማዘመን ሥራ እየከወኑ የ1888ን የአድዋ ጦርነትን ተጋፍጠው በድል ተወጡ።

ጣሊያን በጦርነቱ በተሸነፈች በማግስቱ የአዲስ አበባ ስምምነት የተባለውን ውል በመፈረም የኢትዮጵያን ነፃና ሉዓላዊ ሀገርነት ሳታቅማማ ተቀበለች፤ ኤምባሲዋንም ከሁሉም ቀድማ ከፈተች። በመቀጠልም ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ ቤልጂየም፣ ራሺያና ሌሎችም ሀገሮች ሚሲዮኖቻቸውን በአዲስ አበባ በመክፈት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት መቀበላቸውን አረጋገጡ።

የኤምባሲዎቹ መከፈት ለአዲስ አበባ የመሰረተ ልማት መስፋፋት ትልቅ እድል የፈጠረ ነበር። ንጉሡ ነገሡቱ ከአውሮፓ መንግስታት ጋር ግንኙነታቸውን ይበልጥ በማሳደግ በ1892 የስልክ አገልግሎትንና በጀኔረተር ኃይል የሚሠራ መብራትን፣ የቧንቧ ውሐ፣ ሆስፒታልና ፖሊስ ጣቢያ አስገነቡ። በ1897 ደግሞ የማዕከላዊ ባንክ በማቋም በአገሪቱ የዘመናዊ የፋይናንስ ሥራ እንዲስፋፋ የመሰረት ድንጋዩን አኖሩ። የከተማዋ መሰረተልማትና የፋይናንስ ሥርዓት ፈር እየያዘ መሄድ አዲስ አበባ በአጭር ጊዜ ውስጥ የበርካታ የውጭ አገር ዜጎች፣ ዲፕሎማቶችና ባለሐብቶች መናኸርያ ከመሆን ባሻገርም በከተማዋ የንግድና የኢንቬስትመንት መስክ ለመሰማራት ፍላጎች እያሳዩ እንዲመጡ አስቻለ። ቁጥሩ እየጨመረ ለመጣው የውጭ ሀገር ጎብኚ እንግዳ መሪፊያ በማስፈለጉ የእተጌ ጣይቱ ሆቴል በ1898 ተከፈተ።

የዘመናዊ ትምህርት ፈር ቀዳጅ የሆኑት ዳግማዊ አጼ ሚኒሊክ የዳግማዊ ሚኒሊክ ትምህርት ቤትን በ1899ከማቋቋማቸው በተጨማሪ በፊትአውራሪ ኃብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ዋና ሚኒስትርነት (በአሁኑ አጠራር ጠቅላይ ሚኒስትርነት እና የጦር ሚኒስቴርነት) የሚመራ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በ1898 ለመጀመሪያ ጊዜ በማቋቋም የዘመናዊ ሀገረ-መንግስት ግንባታቸውን ወደ ላቀ ከፍታ አሸጋገሩት። የመንገዶችና ሌሎችም የመሰረተ ልማት አውታሮች ግንባታ መስፋፋት፤ የመኳንንቱ ከተለያዩ አካባቢዎች በተለይም ከሰሜን ሸዋ ወደ አዲስ አበባ በስፋት መምጣት፤ የውጭ አገር ዜጎች በብዛት ▶



▶ መግባትና በተለያዩ የንግድና ኢንቬስትመንት ሥራዎች ላይ መሰማራት የአዲስ አበባን ገጽታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቀየረው።1886 ተጀምሮ በ1909 የተጠናቀቀው የኢትዮ ጅቡቲ የባቡር መስመር ደግሞ ይበልጥ የከተማዋን የንግድ ማዕከልነት እያሰፋውና አገሪቱ ምርቶቿን ለውጭ ገብያ እንድትልክ እንደዚሁም በስፋት እድታስገባ ምቹ ሁኔታ ፈጠረ።

ይሁን እንጂ ከ1901 ጀምሮ የንጉሡ ነገሥቱ ጤንነት ከዕለት ወደ ዕለት በዕጅጉ እያሽቆለቆለ መምጣት የአገሪቱ አንድነት ላይ ከፍተኛ ስጋት እየጋረጠ መጣ። በተለይ ንጉሡበሕይወት ያለ አልጋ ወራሽ ልጅስላልነበራቸው የሥልጣን ክፍተቱ እንዴት ይሞላል የሚለው አውሮፓውያኑን ጭምር ያሳሰበና ሀገሪቷን ለሶስት ተከፋፍሎ ለመቀራመት ድርድር ያስቀመጠ ክስተት ነበር። የልጅ ልጃቸው ልጅ እያሱ በ1905 በትረ ሥልጣኑን በመረከቡና በሸዋ መኳንንቶች ዘንድ የተሰጋው የመከፋፈል አደጋ በመቅረቱ ጣሊያ፣ ፈረንሳይና እንግሊዝ ኢትዮጵያን ለሶስት ለመቀራመት እንደቋመጡ አስቀርቷቸዋል።

ፍላጎቱ ከምስራቁ የአገሪቱ ሕዝቦች ጋር የሻከረውን ግንኙነት ማለዘብ ላይ ያደረገው ልጅ እያሱ አጼ ሚኒሊክ የጀመሩትን ሀገር የማዘመን ታላቅ ፕሮጀክት የማስቀጠል አቅምና ፍላጎት እምብዛም አልነበረውም። ይልቁንም ባልተለመደ መልኩ የተለያዩ ሚስቶች ከአፋር አካባቢ ማግባቱ በቤተ መንግሥቱ ዙሪያ የነበሩ የኃይማኖት መሪዎችንና የሸዋ መኳንንቶችን አላስደሰተም ነበር። በመሆኑም በይፋ የንጉሠ ነገሥትነት አክሊልን ሳይደፉ የያዘውን በትረ ስልጣን ከሶስት አመት በላይ ሳይቆይበት እንዲያጣው ሆነ። በምትኩም የአጼ ሚኒሊክ ሴት ልጅ ዘውዲቱእንዲነግሱ በማሰብ፤ ልጅ እያሱ ከስልጣናቸው መስከረም 17፤ 1908 እንዲነሱ ተደረገ።

ሐረር የተወለዱት ንግሥት ዘውዲቱበመንግሥት አስተዳደር ኃላፊነት እምብዛም ልምድ ስለሌላቸው ክፍተቱን ለመሙላትበንግሥናው የዘር ሐረግ መሰረት ቀጣዩን አልጋወራሽ ልዑል ተፈሪ መኮንን ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ (Regent Pleni-potentiary) በዘመኑ አጠራር ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው አብረዋቸው እንዲሠሩ የሸዋ መኳንንቶች አመቻቹ።ለ14 ዓመት ያህል በነገሡበት ዙፋን ወግ አጥባቂና ሃይማኖተኝነት የሚጫናቸው ንግሥት ዘውዲቱ በርካታ ቤተክርስቲያን ከማሠራት አልፈው በከተማዋና አገሪቱ የነበራቸው የልማት አሻራ እብዛም ነበር። ልዑል ተፈሪ መኮንን ግን የዳግማዊ አጼ ሚኒሊክን ፈለግ በመከተል በዘመናዊ ሀገር ግንባታና የልማት ሥራዎች ላይ ተጠምደው ነበር።በተላይ በባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴነት ዘመናቸው መገባደጃ አካባቢ የአገሪቱን የወጭ ንግድ በማሳደግ በተለይም ቡና፣ ቆዳናየቆዳ ውጤቶችን ወደውጭ በስፋት በመላክ በሀገሪቱ የከበርቴው ሥርዓት እንዲያቆጠቁጥ መንገድ ከመከፈቱም ባሻገር በከተማው የተፈሪ መኮንን ድጋፍ እንዲጎለብት ከፍተኛ አስተዋፆ አድርጓል።በዘውዲቱ የመጨረሻዎቹ ዓመታት በጉልህ ሚናቸው እየጨመረ የመጣው ተፈሪ መኮንን ኢትዮጵያን በ1916 የሊግ ኦፍ ኔሽን አባል በማድረግና ከአውሮጳመንግሥታት ጋር የጠበቀ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በመፍጠር ሀገር ለማዘመንና በአውሮጳውያን ዘንድ ያለውን የኢትዮጵያ ገጽታ ለማሳደግ ባበረከቱት አስተዋፆ በይበልጥ ይታወቁ ነበር። ተፈሪ ከሀገር ውጭ ለኦፊሴላዊ የሥራ ጉብኝት የሄዱ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ መሪም ናቸው።

‹‹በዘውዲቱ የመጨረሻዎቹ ዓመታት በጉልህ ሚናቸው እየጨመረ የመጣው ተፈሪ መኮንን ኢትዮጵያን በ1916 የሊግ ኦፍ ኔሽን አባል በማድረግና ከአውሮጳመንግሥታት ጋር የጠበቀ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በመፍጠር ሀገር ለማዘመንና በአውሮጳውያን ዘንድ ያለውን የኢትዮጵያ ገጽታ ለማሳደግ ባበረከቱት አስተዋፆ በይበልጥ ይታወቁ ነበር። ››

በ1923 ንግሥቲቱ በድንገት ሲያርፉ፣ ተፈሪ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተብለው የንጉሠነገሥትነት አክሊል ደፉ።ተፈሪ ሊነግሡ ዕቅድ ከተያዘበት ጥቂት ሳምንት በፊት የአዲስ አበባን ገጽታ የማስዋብ ሥራ ማለትም መንገዶቿን የማጽዳትና ቀለም የመቀባት፣ ▶


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema



የኢትዮጵያ ዜጎች
ለማኅበራዊ ፍትህ
(ኢዜማ)

ነሐሴ 24 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

የመብራት፣ ውሐና የስልክ አገልግሎቶችን የማስፋት እንደዚሁም በርካታ ኃውልቶችን በከተማው የማስቆም ሥራ ተሠርቷል። በአጭር ጊዜ ውስጥ ቢሆንም የተስፋፋው የልማት ሥራ የተፈሪን መንገሥየከተማው ሕዝብ በከፍተኛ ተስፋ እንዲጠብቀው አድርጓል።

ንጉሠነገሥቱ ሀገሪቱን የማዘመን ሥራ ከሜጂ ጃፓን የተቀዳ ሕገ-መንግስት በራሳቸው ፍላጎት በ1923/4 ለሀገሪቱ በማስተዋወቅ የዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር እንዲጎለብት አንድ እርምጃ ወደፊት ሄደዋል።ሀገሪቱ በጣልያን እስከተወረረችበት ጊዜ ድረስም በርካታ መሰረተ ልማቶችን በተለይም የትምህርት ተቋማትን በማስፋፋት የአዲስ አበባንና የሌሎች ከተሞችን እድገት ወደፊት አስቀጥለዋል።

## የአምስት ዓመቱ የጣልያን ወረራ (1928 - 1935)

የአድዋ ድልን ለመበቀል ሁሌም ታሴር የነበረችው ጣሊያን በ1917 የእብሪተኛው ቤኔቶ ሙሶሊኒ ወደ ሥልጣን መምጣት አጋጣሚውን አመቻቸላት። በሶማሊያና ኤርትራ የቅኝ ግዛት አስተዳደር የነበራት አውሮጳዊቷ ሀገር በ1928 ወል ወል በተባለው የኢትዮጵያ የምስራቅ ግዛት በድንገት ጥቃት በመዘንዘር የጀመረችው ወረራ ጉዳዩ ጠብ ያለሽ በዳቦ ሆኖ ጭራሽ ኢትዮጵያ ይቅርታ እንድትጠቅይና ካሳ እንድትከፍል በይፋ እስከመጠየቅ ደረሰች። ጉዳዩን ወደ ሊግ ኦፍ ኔሽንስ የወሰዱት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (ቀ.ኃ.ሥ)የመንግሥታቱን ድርጅት ምላሽ እየተበቁ ባለበት ሰዓት ጣሊያን ወረራዋን እጅግ በታጠቀ ግዙፍ ወታደርና ከአየር ላይ በሚወረወር የመርዝ ጋዝ በመታገዝ በቅድሚያ አድዋን በማውደም፤ ከዛም አክሱምንበመደበደብ። ፊታቸውን ወደመቀሌን በማዞርእስከማይጨው ዘለቁ። በማይጨው የንጉሠነገሥቱን ዋና የተደራጀየሚባል ጦር አሸንፈው ሚያዚያ 27 ቀን 1928 አዲስ አበባን ተቆጣጠሩ።በመኳንንቱ ጎትጓችነት የጣሊያን ጦር አዲስ አበባ ከመግባቱ ሶስት ቀን ቀደም ብለው ቀ.ኃ.ሥ ወደ እንግሊዝ ተሰደዱ።

የጣሊያን የአምስትዓመቱ ወረራ በርካታ ጉዳቶችን ያስከተለ ቢሆንም፤ ከመሰረተ ልማት ማስፋፋት ጋር በተያያዘ ለአዲስ አበባም ሆነ ለሌሎች የአገሪቱ ከተሞች ትልቅ እመርታን አምጥቷል። በአዲስ አበባ ከፍተኛ የሆነ የመንገድና የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ በተለይም ወረራውን ተከትሎ የመጡ የጣሊያን ዜጎች በሚኖሩባቸው የከተማው አካባቢዎች ተስፋፍቷል።እንደዚሁም በመላ ሀገሪቱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በከፍተኛ ፍጥነት ተስፋፍተዋል። ይህም ከተማዋንና የአገሪቱን እድገት በከፍተኛ ደረጃ አሻሽሎታል። አራዳ ጊዮርጊስ አካባቢ የነበረውም የገበያ ቦታ ወደ መርካቶ በማዞር የአፍሪካ ሰፊ ክፍት የገብያ ማዕከል እንዲፈጠር አስተዋፆ አድርጓል፤ በአራዳ ጊዮርጊስ አካባቢ ደግሞ ዘመናዊ ምግብ ቤቶች የኬክና ሌሎችም ፈሳሽ መጠጦችን እና ምግብ የሚያቀርቡ የመዝናኛ ቤቶች መስፋፋት ለከተማው መዘመንና ማደግ አስተዋፆ ነበራቸው።

ሙሶሊኒ ከሂትለር ጋር በማበር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተሳታፊ በነበሩት ፈረንሳይና እንግሊዝ ላይ ወረራ በማወጁ የእንግሊዝ መንግሥት የኢትዮጵያን ወረራ ትኩረት በመስጠት ጣሊያንን ከኢትዮጵያ ለማስወጣት ጦሯን በሱዳን፣ ኤርትራና ሶማሊላንድ በኩል አዘመተች። በስተመጨረሻም ከአምስት ዓመት የስደት ቆይታ በኋላ ቀ.ኃ.ሥ በሱዳን በኩል አድርገው ሚያዚያ 27/1933 አዲስ አበባ ገቡ።

## አዲስ አበባ በዘመነ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ከጣሊያን ወረራ በኋላ (1933 – 1966)

ቀ.ኃ.ሥ ወደ አዲስ አበባ ከተመለሱ በኋላ አዲስ አበባ በሁሉም አቅጣጫ መስፋፋቷንና በአጎራባች መንደሮች የሚኖሩ አርሷደሮችን ማፈናቀሏን ቀጠለች። በተለይ ለመንገድ ግንባታና ዘመናዊ የመንግስት ተቋማት ቢሮዎች እንደዚሁም ዘመናዊ ህንፃዎችና የገብያ ማዕከላት ግንባታና ማስፋፊያ ቁጥሩ ቀላል የማይባል ሕብረተሰብ ተፈናቅሏል።

ንጉሡ ከተማዋን ከተቆጣጠሩ በኋላ ያለማቋረጥ ለሃያ ተከታታይ ዓመታት ከተማና ሀገር ግንባታቸውን አስፋፍተው ቀጠሉ። በዚህም የማዕከላዊውን መንግስት ሥልጣን ይልጥ በማደላደልና ከፊውዳል ስርዓት ቀስ በቀስ በማላቀቅ የከበርቴው ስርዓት እዲስፋፋ ጥረት አድርገዋል፡፡ ለዚህም የዘመናዊና ደሞዝ ተከፋይ የመንግሥት ስራተኛ (ሲቪል ሰርቪስ) እንዲስፋፋ ጥረት አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም በ1935 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን፤ በ1936 የአዲስ አበባ ንግድ ስራ ኮሌጅን፤ በ1937 የኢትዮጵያ አየር መንገድን፤ በ1942 የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲን፤ በ1947 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር፤ በ1955 የፖሊስ ኦርኬስትራ የሙዚቃ ቡድንን በማቋቋም ለከተማውና አገሪቱ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፆ አበርክተዋል። ቁጥር ስፍር የሌለው የትምህርት ተቋማትንም በአዲስ አበባና በተቀረው የሀገሪቱ ክፍል አስፋፍተዋል።

ምንም እንኳን የነዋሪዎች መፈናቀል ትቶ ያለፈው የታሪክ ጠባሳ ቢኖርም እየተስፋፋ የመጣው ግንባታ የከተማዋን ዘመናዊነትና ዓለማቀፋዊነት እየጨመረው በመሄድ አዲስ አበባ በሂደት በአፍሪካ ጉዳዮች ላይ ወሳኝ ድርሻ የምትጫወት ከተማ እየሆነች እንድትሄድ ከፍተኛውን የመንገድ ጥርጊያ አድርጓል።ንጉሡ ከነዊንስተን ቸርችል፣ ቻርለስ ደጎልና አይዘን አወር ጋር በቅርበት በመሥራት ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታትን ከመሰረቱ 50 ሀገራት አንዷና በነፃነት የምትገኝ ብቸኛ አፍሪካዊትመስራች ሆናለች፡፡ ንጉሡከዓለም ኃያላን ሀገራት ጋር የነበራቸው የጠበቀ ወዳጅነት የአፍሪቃ ጉዳዮችን ትኩረት እንዲሰጣቸውና የፀረ-ቅኝ ግዛት አጀንዳቸውም ሰሚ እንዲያገኝ ረድቷል። በዚህም አዲስ አበባ በ1951 የተቋቋመውን የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ የኢኮኖሚ ኮሚሽን መቀመጫ እንድታስተናግድ እድል ሰጥቷታል።

ሀገሪቱ በጣሊያን ዳግም ወረራ ወቅት የተሸነፈችበት ዋነኛ ምክንያትጣሊያን በአየር ድብደባ የበላይነት ይዞ ስለነበር ቀ.ኃ.ሥ በተለይ ዘመናዊ የአየር ኃይል የመገንባት አጀንዳን ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ሰርተዋል። የአየር ትራንስፖርትን አስፈላጊነት በመገንዘብም በ1937 ለሲቪሊያን አገልግሎት የሚሰጥ የኢትዮጵያ አየር መንገድን መስርተዋ። የአየር መንገዱ መመስረት አዲስ አበባን ከበርካታ የአፍሪካና አውሮጳከተሞች ጋር የማስተሳሰሩ ፋይዳ ለከተማዋ ዘመናዊነት ትልቅ ሚና ተጫውቷል። በተለይ የኤርፖርቱ ከቀረጥ ነፃ ንግድ በተነፃፃሪየዳበረ በመሆኑ ከነፃነት በኋላ የመጡ በርካታ የአፍሪካ መሪዎች ከቀረጥ ነፃ ለመሸመት ወደ ከተማይቱ ይመጡ ነበር። ይህም የከተማዋን አለማቀፋዊ የጉዞ መዳረሻነት እየጨመረው መጥቷል።

የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ኮሌጅ መቋቋምን ተከትሎ እንደዚሁም ንጉሠ ነገሥቱ ለተለያዩ የአፍሪካ ሀገሮች ተማሪዎች 200 የነፃ ትምህርት ዕድል በመስጠታቸው ከተማዋ ለተቀረው የአፍሪካውያን መናኸሪያነት ራሷን ማዘጋጀት ተያያዘችው።በኋላም በ1950ዎቹ የአፍሪካ ሀገሮች የሚያደርጉትን ከቅኝ ግዛት የመላቀቅ ጥረት በማገዝ እንደዚሁም በሁለት ጎራ ተካፍለው የነበሩትን ነፃ የወጡ የአፍሪካ አገሮች በማቀራረብ የአፍሪካ አንድነት ▶



▶ ድርጅትን በግንቦት 17 ቀን 1955 በአዲስ አበባ እንዲቋቋም ከፍተኛ ሚና ተጫወቱ። በዚህም የአዲስ አበባን የአፍሪካ የዲፕሎማሲ መናኸሪያነት እንዲጎለብት አደረጉ።

ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ተማሪዎች በጊዜ ሂደት የዓለማቀፉ የኅብረተሰባዊ ንቅናቄ (socialist movement) ትኩረታቸውን እየሳበና በሀገራቸው ውስጥ ሳይቀረፍ ለረጅም ጊዜ የቆየውና አርሷደሩን ጭሰኛ ያደረገ ኋላ ቀር የመሬት ስሪት እንደዚሁም ባለው የማዕከላዊና አሃዳዊ ስርዓት ውስጥ ብዝሃነትን ማስተናገድ አለመቻል የብሔር ጥያቄ በየቦታው በተለይም በተማሪዎቹ ተነሳ። ሪፖብሊካዊና ዴሞክራሲያዊ የሕዝብ መንግሥት እንዲቋቋም የዩንቨርሲቲ ተማሪዎቹ የሚያደርጉትትግል እየበረታ ሄዶ ረጅሙ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ግብዓተ መሬት አጣደፈው፡፡ በ1966 በወሎ የነበረው የከፋ ድርቅና በአረብ-ኢስራኤል ጦርነት ምክንያት የነዳጅ ዋጋ መጨመር ሁኔታዎችን አባብሶ ከተማዋ በለውጥ ፈላጊዎቹ ተማሪዎች እንድትታመስ አስገደዳት።

የለውጥ ፈላጊዎቹ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች በተደራጀ መልኩ ሀገር ማስተዳደር በሚያስችል ቁመና ላይ ስላልነበሩ ክፍተቱ የሀገሪቱ ጦር እንዲቆጣጠረው ዕድልፈጠረ። በዚህም የ1966 አብዮትን ተከትሎሀገሪቱ በወታደራዊ ዕዝ ስር ወደቀች።

## አዲስ አበባ በ17 ዓመቱ የደርግ ወታደራዊ አስተዳደር

የዩንቨርሲቲ ተማሪዎቹ የነሷቸው የመሬት ላራሹ፣ የብሔር ብሔረሰቦች መብት ይከበር የሚለውናየሕዝባዊ መንግሥት አሁኑኑ ይመስረት ሲሉ ያነሷቸውን አንገብጋቢ ጥያቄዎች ባግባቡ መልስ የሚሰጣቸው የተደራጀ አካል ባለመኖሩ ባልታሰበ ሁኔታ ሥልጣን በወታደር እጅ ወደቀ። ሕዝባዊ ጥያቄው መልስ ሳያገኝ በመቅረቱ በርካታ የፖለቲካ ኃይሎች ነፍጥ አንግበው ጥራኝ ዱሩ ሲሉ ጫካ ገቡ።

ከዚህ ቀደም ብሎ ንጉሡ ከኤርትራ ጋር የነበረውን ፌዴራሽን በጉልበት በማፍረሳቸው ድርጊቱን ተቃውመው ጫካ የገቡ ኃይሎች በትጥቅ ትግል ኤርትራን ለመገንጠር የሚታገሉ ኃይሎች ወታደራዊው መንግስት ሳይርጋጋና አገር የማስተዳደር ዕቅድ ሳያዘጋጅ ከየአቅጣጫው ውጊያ ገጠሙት። ደርግ አስራ ሰባቱን አመታት የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ለማስጠበቅ ነው በሚል ሰበብ ብዙ ህይወት አጥፍቶ፤ ለልማት የሚውለውን ውስን የአገር ኃብት አባክኖ በ1983 ከስልጣን ወረደ። በመሆኑም አዲስ አበባ በዘመነ ደርግ ካስተናገደችው በርካታ ሰላማዊ ሰልፎች፣ ጉባዔዎችና ኃውልቶች የዘለለ ይህ ነው የሚባል የልማት ትሩፋት በደርግ ዘመን አላገኘችም።

## አዲስ አበባ ከ1983 ወዲህ

ግንቦት 20 ቀን 1983 ኢሕአዴግአዲስ አበባን እንደተቆጣጠረ ከተማዋን ክልል 14 ተብላ በሽግግር መንግሥቱ ቻርተር ዕውቅና ተሰጥቷት ራሷን በራሷ የምታስተዳድር የክልልነት ደረጃ የነበራት ከተማ ሆነች። ነገር ግን በ1987 በፀደቀው ሕገመንግሥት ነገሮች

> ‹‹ሕገመንግሥቱ ከነችግሩም ቢሆን የአዲስ አበባ ሕዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብቱ የተጠበቀ እንደሆነ በግልጽ አስቀምጧል። ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ሕዝብ ባላፉት 25 ዓመታት የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች ከሚያስተዳድሯቸው ክልሎች በሚልኳቸው የከተማዋን ሕዝብና ስነ-ልቦና በማይረዱ ካድሬዎች ስትመራ ቆይታለች።››

ተቀያይረው አገሪቱ በዘጠኝ ክልሎችና ሁለት የከተማ መስተዳደር ስትዋቀርአዲስ አበባ ቀድሞ የነበራትን የክልልነት ደረጃአጣች። የፌደራል መንግሥቱ መቀመጫ ብትሆንም የከተማው ሕዝብ በተፈጥሮ ያገኘውን ዴሞክራሲያዊ መብቱ ተነፍጎ ባልተለመደ ሁኔታ የከተማው አስተዳደር ተጠሪነቱ ሥልጣን በምርጫ ለሰጠው ሕዝብ መሆኑ ቀርቶ ለፌደራል መንግሥቱ እንዲሆን እና የከተማው ሕዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብቱን የሚገድብ ኢዲሞክራሲያዊ የሆነ ውሳኔ ሕገመንግስቱን በማርቀቅ ሂደት ተወሰነ፡፡ ይህ ታሪካዊ ስህተት የሀገሪቱ ፖለቲካ ከፍተኛ ውጥንቅጥ ውስጥ እንዲገባ ያደረገ ትልክ የፖለቲካ ሴራ ነው።

የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 49 ንዑስ ቁጥር 3 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነቱ ለፌደራል መንግሥቱ ነው የሚለው አንቀጽ የከተማውን ነዋሪ የልኡዋላዊ ሥልጣን ባለቤትነት መሆኑንጥያቄ ውስጥ የሚከት ጉዳይ ነው።በተጨማሪም በንዑስ ቁጥር 5 ላይ የሰፈረው የኦሮሚያ ክልል በከተማው ላይ ያለው ልዩ ጥቅም ይጠበቅለታል የሚለው አጨቃጫቂና በየጊዜው ያልተፈለገ ክርክር ውስጥ የሚጥል ሃሳብ በሕገመንግሥቱ መስፈሩ ከተማዋ አሁን ለተጋረጠበት የባለቤትነት አወዛጋቢ ጥያቄ መነሻ ሆኗል።

ሕገ መንግሥቱ አዲስ አበባ በኦሮሚያ ውስጥ የምትገኝ መሆኗን በመጥቀስ የልዩ ጥቅም ጉዳይ ከዚህ እንደሚመነጭ ማስቀመጡ አንደኛ የከተማዋን ራሷን የቻለችና ነዋሪውም የሙሉ መብት ባለቤትነቱን የሚጋፋ የሕግ ክፍተት ሲሆን፤ አጠቃላይ የአገሪቱን ፖለቲካ ውዝግብ ያልተለየው እንዲሆን የዳረገውም ይኸው የልዩ ጥቅም ጉዳይ ነው።

ሕገመንግሥቱ ከነችግሩም ቢሆን የአዲስ አበባ ሕዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብቱ የተጠበቀ እንደሆነ በግልጽ አስቀምጧል። ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ሕዝብ ባላፉት 25 ዓመታት የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች ከሚያስተዳድሯቸው ክልሎች በሚልኳቸው የከተማዋን ሕዝብና ስነ-ልቦና በማይረዱ ካድሬዎች ስትመራ ቆይታለች። ይህም ከፍተኛ የአመራር ክፍተት ከመፍጠሩም በላይ ከስድስት ሚሊዮን የሚበልጠውን የከተማው ሕዝብ በከተማው ጉዳይ ላይ ባይተዋር እንዲሆን አድርጎታል። ከዛም ባለፈ ከተማዋ በሙስናና ብልሹ አሠራር እንድትታመስ ዋነኛ ምክንያት ሆኗል። አዲስ አበባ በአዲስ አበቤዎች (በከተማዋ ባይወለዱም አብዛኛው እዴሜያቸውን ያሳለፉ የከተማዋን ስነ-ልቦናና ከተሜያዊ ማንነት በሚያውቁና በሚረዱ እንደዚሁም ከተማዋን የሚመጥን ዓለምአቀፋዊ የከተሞች ተሞክሮ በቀሰሙ መሪዎች) መተዳደር አለመቻሏ በርካታ የልማት ፕሮጀክቶች ከፍተኛ የአፈፃፀም ዝርክርክነትና ከተቆርቋሪነት ስሜትና አቅም ማጣት የሚመነጩ የጥራት ቁጥጥር ማነስ ችግር በርካታ የልማት ፕሮጀክቶች እዴሜያቸው አጭር፣ ወጪያቸው የትየለሌ፣ ጥራታቸው ዝቅተኛ እደዚሁም የህብረተሰብ ችግርን ከመፍታትና ለከተማዋ ዕድገት ከሚያበረክቱት አስተዋፆ አንፃር ሚናቸው አናሳ እንዲሆኑ አስተዋፆ አድርጓል። የሙስናና የኃብት ብክነቱ ችግር ደግሞ የባሰ ነው፡፡

በመሆኑም አዲስ አበባ የከፋ ድህነት ከተንሰራባቻቸው የአገራችን ከተሞች ሁሉ የባሰና ውስብስብ ችግር ያሉባት ከተማ ▶

▶ መሆኗ አለም ዐቀፍ ሚና ያላትን ዋና ከተማ ሚናዋን የሚያኮስስ አሳዛኝ ዕውነታ ነው።

### የከተማዋ መስፋትና ኢፍትሃዊው የአርሷደሮች መፈናቀል

አዲስ አበባ በዘመነ ኢህአዴግ በሁሉም አቅጣጫ ሰፍታለች፤ ዓይነተ-ብዙ የመሰረተ-ልማት አውታሮችና የመሰረታዊ አገልግሎቶች በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍተዋል፡፡ በተለይ በመንግሥት የሚሰሩ የጋራ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ በ1996 ከተጀመረ ወዲህና የግል የመኖሪያ ቤት አልሚዎች በመስፋፋታቸው ከተማዋ በከፍተኛ ደረጃ ሰፍታለች፡፡ ይህም በአጎራባች የኦሮሚያ ክልል የሚገኙ አርሷደሮች ያለበቂ ካሳ ሕይታቸውን በሚያመሰቃቅል፣ ማኅበራዊ ትስስራቸውን በሚያጠፋና በሀገሪቱ ማኅበራዊ ፍትህን በሚያቀጭጭ ሁኔታ ለዘመናት ከኖሩበት ቀዬ እንዲፈናቀሉ ተደርጓል፡፡

ይህ በሕግም፣ በሞራልም ሆነ በሰብዓዊነት ሚዛን ያልተገባ በመንግሥት የተፈፀመ የቀማኛነት ሥራ የከተማዋ አጎራባች አርሷደሮችን ብቻ ሳይሆን የከተማዋንም መሐል ነዋሪ ሰለባ አድርጓል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ በልማትና ከተማን መልሶ ማደስ በሚል ስም በሺዎች የሚቆጠሩ የከተማውን ነዋሪዎች ያለበቂ ካሳ እንዲፈናቀሉና በከተማው ዳርቻ የመሰረተ-ልማት አቅርቦትባልተሟሉባቸውና የኑሮ ዋስትና ባልተረጋገጠባቸው አኳኋን በከተማው ዳርቻ እንዲሰፍሩ አድርጓዋል፡፡ በተቃራኒው ከመንግሥት ሹመኞች ጋር የጥቅም ተጋሪ የሆኑ ባለሃብቶች በከተማው ውስጥ ቁልፍ የሆኑ ቦታዎችን ዝቅተኛ የሊዝ ዋጋ እየከፈሉ አንዳንድ ጊዜም ምንም የሊዝ ዋጋ ሳይከፈል ድሃ ይኖርባቸው የነበሩ ቦታዎችንእንዲቀራመቱ ተደርጓል፡፡ ይህም ጥቂት ኃብታሞች የከተማውን ኅብረተሰብን ችግር የሚፈታና ኑሮ የሚያቀል እንደዚሁም ለዜጎች ሥራ በሚፈጥር ሁኔታ አዲስ ምርትና አገልግሎት ወደ ገበያ በማስገባት ሳይሆን ምንም ሳይለፉ፣ ሳይደክሙና ሳይጨነቁ በአቋራጭ ከሙሰኛ ባለሥልጣናት ጋር በመሞዳሞድ በኢኮኖሚው ውስጥ ምንም ዓይነት አዲስ ዕሴት ሳይፈጥሩ መሬት በመቸብቸብ ብቻ ኃብት እንዲያከማቹ መንገድ ከፍቷል፡፡ በዚህም ምክንያት በከተማው የሚስተዋለው የገቢ ልዩነት በከፍተኛ ሁኔታ መስፋትና ለአብዛኛው የከተማው ነዋሪ አልቀመስላለው የኑሮ ውድነት ከፍተኛ አስተዋፆ አድርጓል፡፡

በከተማው ውስጥም ሆነ በአጎራባች የኦሮሚያ ክልል የሚኖሩ አርሷደሮችን በግፍ የሚፈናቀሉበት ዋነኛ ምክንያት አንዱ የከተማዋ በቅጡ ያልተጠናና በብቁ ባለሙያዎች የማይተገበሩ የከተማዋ ማስተር ፕላን ነው፡፡ መንግሥታዊ የመሬት ዝርፊያን ወደከፍተኛ ደረጃ የሚያደርስ የነበረው 10ኛው የአዲስ አበባ የተቀናጀ ልማት ማስተር ፕላን የከተማዋን ስፋት በ100ኪ.ሜ ራዲየስ በመለጠጥ አዲስ አበባን እጅግ ትልቅ ከተማ የሚያደርጋት የነበረ ሲሆን፤ ተተግብሮ ቢሆን ኖሮ የሚያፈናቅለው የአርሷደር ብዛት የትየለሌ ይሆን ነበር፡፡ በመሆኑም ይህ የከተማዋ ዕቅድ በ2008 እንደሚተገበር በተዋወቀ በማግስቱ በዩንቨርሲቲ በሚማሩ የኦሮሚያ ወጣቶች ክፉኛ ተቃውሞ ገጠመው፡፡ ተቃውሞውም ከዕለት ወደዕለት እየሰፋና መልኩን እየቀየረ ሄዶ በክልሉ የመሪዎች ለውጥ እንዲደረግ ምክንያት ሆኗል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከክልሉ ባለሥልጣናት ጋር ተመካክረው ማስተር ፕላኑ እንዲቀርና የፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ጽ/ቤቱም እንዲዘጋ ቢያደርግም የወጣቶቹ ተቃውሞ ወደአጠቃላይ የሥርዓት ለውጥ ወደመሻት በመሸጋገሩ ተቃውሞው ተባብሶ ቀጠለ፡፡ ይባስ ብሎም ወደ አማራና የደቡብ ክልል ተዛመተ፡፡ ይህም ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ የካቲት 2010 ላይ የሥልጣን መልቀቂያ ደብዳቤ እንዲያስገቡ ምክንያት ሆነ፡፡ በምትካቸውም ዶ/ር ዐቢይ አህመድ መጋቢት 24 ቀን 2010 ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙ ሲሆን ኢትዮጵያም በአዲስ የፖለቲካና ሁሉን ዓቀፍ ሥርዓት የለውጥ ለማድረግ ጉዞ እድትጀምር መነሻ ሆኗታል፡፡

### የአዲስ አበባ ዕድገትና የኦሮሚያ ልዩ ጥቅም ጉዳይ

የአዲስ አበባ ማደግና መስፋት ለአጎራባቾቿ የኦሮሚያ አርሷደሮች ዕድልም፤ ስጋትም ነው፡፡ ከተማዋ እስካሁን በመጣችበት አርሷደሮችን ኢፍትሃዊ በሆነ መንገድ የማፈናቀል ሂደት ከቀጠለች የከተማዋ ዕድገት በርግጥም ለአርሷደሮቹ ስጋት ነው፡፡ ምክንያቱም አርሷደሮቹ መሬታቸውን የለበቂ ካሳና የሥራ ዋስትና ስለሚነጠቁ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ዜጎችን ያለበቂ ካሳ፣ ከተፈናቀሉ በኋላ በሚሰፍሩባቸው አዲስ መንደሮች የመሰረተልማት አቅርቦት ሳይሟላና የኑሮ ዋስትናቸው ሳይመቻች ከቀያቸው የማፈናቀል ተግባር ሀገሪቱን ለማኅበራዊ ቀውስና የፖለቲካ ችግር የሚዳርግ በመሆኑም ስጋትነቱ ከአርሶ አደሮቹ አልፎ ለመላ ሀገሪቱ ነው፡፡

ነገር ግን ከተማዋ በሥርዓትና በወግ እንድታድግ ከተደረገ፣ በዙሪያዋ የከበቧትን

> ‹‹ ከተማዋ እስካሁን በመጣችበት አርሷደሮችን ኢፍትሃዊ በሆነ መንገድ የማፈናቀል ሂደት ከቀጠለች የከተማዋ ዕድገት በርግጥም ለአርሷደሮቹ ስጋት ነው፡፡ ምክንያቱም አርሷደሮቹ መሬታቸውን የለበቂ ካሳና የሥራ ዋስትና ስለሚነጠቁ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ዜጎችን ያለበቂ ካሳ፣ ከተፈናቀሉ በኋላ በሚሰፍሩባቸው አዲስ መንደሮች የመሰረተልማት አቅርቦት ሳይሟላና የኑሮ ዋስትናቸው ሳይመቻች ከቀያቸው የማፈናቀል ተግባር ሀገሪቱን ለማኅበራዊ ቀውስና የፖለቲካ ችግር የሚዳርግ በመሆኑም ስጋትነቱ ከአርሶ አደሮቹ አልፎ ለመላ ሀገሪቱ ነው፡፡ ››

አርሷደሮች በበጎ ጎኑ ሕይወታቸውን በሚለውጥ መልኩ የከተማዋ ማደግና መስፋት እነሱንም በሚጠቅምና በምንም መልኩ የበይ ተመልካች በማያደርግ አካሄድ ከተከናወነ ሂደቱ ለሁሉም መልካም ዕድል ይፈጥራል፡፡ በዚህ ሂደት አዲስ አበባ ባደገችና የኢኮኖሚ ዕንቅስቃሴዋ በዛው ልክ በሰፋ ቁጥር የምትፈጥረው የገበያ መጠን እያደገ ይሄዳል፡፡ ይህም በከተማው የሚኖረው ኅብረተሰብ ቁጥሩ እንዲጨምርና የመግዛት ፍላጎቱና አቅሙ እንዲያድግ ያደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ ትልቅ የገበያ አቅም ስለሚፈጥር በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል ከሚኖር አርሷደር ይልቅ ይበልጥ ለዚህ ትልቅ ገበያ ምርቶቹን በማቅረብ ተጠቃሚ የመሆን ዕድል የሚኖረው በቅርብ የሚገኘው የኦሮሚያ አርሷደር ይሆናል ፡፡ ይህ ማለት በዙሪያዋ ያለው የኦሮሚያ አርሶ አደር ለትልቁና ሰፊው የአዲስ አበባ ገበያ ባለው ቅርበት ብቻ በትግራይ ካለውም፣ በአማራም፣ ▶



▶ በደቡብም ሆነ በየትኛውም ክልል ከሚገኝ አርሶ አደር የተሻለ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ይህ በርግጥም ሌሎች የአገሪቱ ዜጎች የማያገኙትልዩ ጥቅም ነው፡፡

ይሁን እንጂ እምብዛም በጥንቃቄ ባልተዘጋጁና በቅጡ በባለሙያ በማይተገበሩ የይስሙላ ማስተር ፕላኖች ስትመራ የቆየችው አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿ የውሃ አቅርቦትም ሆነ ከመኖሪያ ቤትና ኢንዱስትሪዎች የሚወጡ የቆሻሻዎች ማጠራቀሚያና ማስወገጃቦታ በኦሮሚያ ላይ ጥገኛ ናት፡፡ ይህ የከተማዋ ራሷን አለመቻል አጎራባች አርሷደሮች ላይ የጤና ዕክል ሲፈጥር አልፎም የሕይወት መጥፋት ጉዳት ሲያስከትል ኖሯል፡፡ በመሆኑም ለአጎራባቾቿ አርሷደሮች ከተማዋ ብዙ መዘዝ አምጥታባቸዋለች፡፡ ይህን ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍና ከተማዋ በኦሮሚያ የከርሰምድር የውሃና ሌላም የተፈጥሮ ኃብት እንዲመናመን በማድረግ ለምታደርሰው ጉዳት ተገቢ ካሳ ማድረግ ይጠበቅባታል፡፡ ኦሮሚያ አዲስ አበባ ላይ የሚኖራት ልዩ ጥቅም (special interest) ከዚህ የመነጨ ብቻ መሆን አለበት እንጂ ከ80 በመቶ በላይ ነዋሪው ኦሮሞ ያልሆነበትን ከተማ የኔነው እስከማለት ሊደርስ አይችልም፡፡

ከተሞችን ከአንድ ብሔር ጋር ማያያዝ የሚቻልም አይደለ፤ ተገቢም አይደለም፡፡ ምክንያቱም ከተሞች ትላልቆቹና በጣም ያደጉቱ ደግሞ በተለይ በባህሪያቸው ዓለማቀፋዊ ጭምር ናቸው፡፡ በዩንቨርሲቲዎቻቸው ከመላው ዓለም የመጡ ተማሪዎችን ያስተናግዳሉ፤ ከመላው ዓለም የመጡ ጎብኚዎችን፣ ዲፕሎማቶችን፣ባለኃብቶችንና የጥበብ ሰዎችን ይይዛሉ፡፡ በመሆኑም እንዲህ ዓይነት ከተሞች የሚኖራቸው ከተሜያዊ ማንነትና ባሕሪ በጊዜ ሂደት ዓለማቀፋዊ (cosmopolitan) እየሆነ ይሄዳል፡፡ አዲስ አበባንም ያየን እንደሆነ የብዘት መጠናቸው ቢለያይም ሁሉም ኢትዮጵያውያን ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ተሰባስበው ይኖሩባታል፤ ዓለማቀፍ ተቋማት በብዛት የሚገኙባት በመሆኗ፣ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች በስፋት ስለሚኖሩና የውጭ ባለኃብቶችም ከየትኛውም የሃገሪቱ ክፍል በላቀ መጠን ስለሚኖሩ የከተማዋ ማንነት ሃገራዊ ከመሆንም አልፎ ዓለማቀፋዊ በመሆን ሂደት ላይ ነው ::

> ‹‹ ሰው በባለቤትነት ላልያዘው ንብረት የሚያደርገው ክብካቤ ውስን በመሆኑ በተለይ የገጠር መሬት በኢኮኖሚው ላይ የሚኖረው እስተዋፆ አናሳ እንዲሆን ያደርጋል፤ ምክንያቱም መሬትን ለብድር ዋስትና ማስያዝስለማይቻል ግብርናውን ለማዘመን የሚያስፈልገውን ፋይናንስ አርሷደሮች በበቂ ሁኔታ ከባንክ እንዳያገኙ ስለሚያደርግ፡፡››

### የ1995 ሕገመንግስት፤ የመሬት ፖሊሲና የዜጎች መፈናቀል

የአዲስ አበባ አጎራባች አርሷደሮች ያለበቂ ካሳ እንዲፈናቀሉ ምክንያት ከሆነው ምክንያቶች ዋነኛው የሀገራችን ሕገመንግስት መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የሕዝብ/የመንግሥት ንብረት ያደረገ መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ዜጎች መሬትን የመጠቀም እንጂ የባለቤትነት መብት የሌላቸው በመሆኑ መንግሥት በፈለገው ሰዓት ከፈለገው ቦታ ዜጎችን በልማት ስም ለማፈናቀል እንዲችል መንገድ ከፍቷል፡፡ በመሆኑም ዜጎች በመሬት ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን የባለቤትነት መብት ለማስጠበቅ ሕገመንግስቱን ማሻሻልና ሌሎችም ዝርዝር የንብረት ሕጎችን ማዘጋጀት ያስገልጋል፡፡ ይህ የዜጎችን መብት ለማስጠበቅ ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳለጥም ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ ሰው በባለቤትነት ላልያዘው ንብረት የሚያደርገው ክብካቤ ውስን በመሆኑ በተለይ የገጠር መሬት በኢኮኖሚው ላይ የሚኖረው እስተዋፆ አናሳ እንዲሆን ያደርጋል፤ ምክንያቱም መሬትን ለብድር ዋስትና ማስያዝስለማይቻል ግብርናውን ለማዘመን የሚያስፈልገውን ፋይናንስ አርሷደሮች በበቂ ሁኔታ ከባንክ እንዳያገኙ ስለሚያደርግ፡፡ ይህም በግብርና ላይ ለተንጠለጠለው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ትልቅ ኪሳራ ነው፡፡

አዲስ አበባ ካሁን በኋላ የሚኖራት ዕድገት ነዋሪዎቿንም ሆነ አጎራባቾቿን በማፈናቀል ላይ እንዳይሆን ኢዜማ ከተማዋን በምርጫ አሸንፎ የሚያስተዳድር ከሆነከሚወስደው ውሳኔዎች አንዱ የከተማዋን ወሰን መለየትና ወሰኗን አልፋ የኦሮሚያን አርሶ አደር በምንም ምክንያት እንዳታፈናቅል ማስቻል መሆን አለበት፡፡ ፓርቲው ከሚከተለው አጠቃላይ የከተማና ቤቶች ልማት ፖሊሲ አንፃር የአጠቃላይ የሀገሪቱ ከተሞች ዕድገት ተመጣጥኖና ሚዛን ጠብቆ እንዲሄድ ስለሚደረግ አዲስ አበባ ተጨማሪ የመኖሪያ ቤት ለመገንባት ወሰኗን አልፋ ኦሮሚያ ውስጥ አትገባም፤ አርሶ አደር አታፈናቅልም፡፡ በተጨማሪም የከተማዋን የቤትም ሆነ የመሥሪያ ቦታ ችግር ለመቅረፍ ከተማዋ ያላትን ውስን መሬት በዘመናዊመንገድ በመጠቀምና ቁመታቸው ረጃጅም ፎቆችን በመገንባት መከናወን ይገባዋል፡፡

ከተማዋ በውሃ አቅርቦትም ሆነ የአካባቢ ስነ-ምህዳር በሚያናጉ የልማት ውጥኖች ኦሮሚያ ላይ ምንም ዓይነት አሉታዊ ተፅኖ እንዳታስከትል ራሷን እንድትችል መደረግ አለበት፡፡ የግድ መጋራት የሚኖርባቸውን የውሃ ግድብና የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታን በተመለከተ ፕሮጀክቶችን ከክልሉ ጋር የተናበበ የጋራ የልማት ፕሮግራሞችን በመንደፍ የከተማዋንም የክልሉንም ሕዝብ ተጠቃሚ በሚያደርግ አግባብ መዘጋጀት አለበት፡፡

### አዲስ አበባ ለምንና እስከመቼ ታጨቃጭቃለች?

ጥቂት የማይባሉ የታሪክ ድርሳናት አሁን አዲስ አበባ ከተንጣለለችበትና የከተማዋ ዕምብርት ከሆነው አካባቢ ብዙም ሳይርቅ በስተደቡብ በኩል በአሁኗ የዱከም ከተማ አካባቢ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን በፊት የተመሰረተች በረራ የምትሰኝ ከተማ እንደነበረች ማስረጃዎች ቢኖሩም፤ ብዙዎች ስለአዲስ አበባ ምስረታ ሲያወሩም ሆነ ሲጽፉ የሚጀምሩት ከእተጌ ጣይቱና ዳግማዊ አጼ ሚኒሊክ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ጀምሮ ስላለው የከተማዋ አመሰራረት ነው።

ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ‘ፊንፊኔ ኬኛ’ የሚለው የአክራሪ ኦሮሞ ብሄርተኞች እንቅስቃሴ እየሰፋና የሀገሪቱን ፖሊቲካ ጡዘት እያከረረው መምጣት የታሪክ ተመራማሪዎች የበረራን ታሪክ አቧራ ለብሶ ከተቀመጠበት ማህደር አንስተው ማገላበጥ እንዲጀምሩ እያደረጋቸው ነው። መገናኛ ብዙኀንም ስለበረራ ታሪክና ምንነት ማንሳትና ዘገባዎችንመሥራት እየጀመሩ ነው።

ለመሆኑ መልሱ ቀላል የሆነው የአዲስ አበባ ባለቤትነት ጉዳይ ስለምን ያጨቃጭቃል? ለሚለው ነባር ጥያቄ መልሱን ከታሪካዊ ሁነቶች ወጣ ባለ መልኩ ከኢኮኖሚ፣ ንግድና ኢንቬስትመንት ፍሰት፣ እንደዚሁም አጠቃላይ የሀገሪቱ የከተሞች እድገትና ስርጭት የተመጣጠነ ካለመሆኑ አንፃር መቃኘት አስፈላጊ ነው።

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ የሁሉም ነገር ▶

> ‹‹የኀች ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ የመሥራት ሕገመንግሥታዊ መብት ነው፤ ነገር ግን ወደ አንድ ከተማ የሚደረግ ያለቅጥ የበዛ ፍልሰት የከተማውን ባሕል፣ የአኗኗር ዘይቤና ከተሜያዊ ማንነት፣ እንደዚሁም የኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ሽሚያ ነባሩ ሕዝብ ላይ የሚያስከትለው ችግር ውሎ አድሮ የፖለቲካና የደህንነት ችግር እስከመሆን መድረሱ አይቀርም።››

▶ ማዕከል፤ የሁሉም ነገር ማጠንጠኛ ዐቢይ ከተማ (prime city) ናት። አሁን ባለው የከተሞች አወቃቀር፣ የልማት ደረጃ፣ የሕዝቦች አሰፋፈር፣ የመሰረተ-ልማት አውታሮች ስርጭት፣ የተሳለጠ የትራንስፖርት፣ የውኃ፣ የኤሌክትሪክ፣ ቴሌኮምና ሌሎችም መሰረተ ልማቶችና አገልግሎቶች ፍትሃዊ ስርጭት፤ የመዝናኛና የመሰረታዊ ፍላጎቶች አቅርቦትን ስንመለከት ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉት የኢትዮጵያ ከተሞች በሚገባው መጠን አላደጉም፤ እንዲያውም ከተማ እንዳይባሉ ብዙ የሚቀራቸውና ያልተሟሉ ግብዓቶች አሉ። መንግሥት ያልተማከለ የከተሞች ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ነድፎ ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉ ከተሞችን የማሳደግ ዕቅድ አዘጋጅቶ ስላልተንቀሳቀሰ አዲስ አበባ በአሁኑ ሰዓት የሁሉም ነገር ማዕከል ናት፤ የንግዱም፣ የፖለቲካውም፣ የስፖርቱም፣ የሚዲያውም፣ የመዝናኛውም፣ የኢንዱስትሪውም፣ የቱሪዝሙም፣ የፋይናንሱም፣ የትምህርቱም፣ የዲፕሎማሲውም፣ የዕስልምናውም፣ የክርስትናውም፣ የሌሎቹም ዕምነቶች፤ ባጠቃላይ የሁሉም ነገር ማጠንጠኛ በመሆኗ እጅግ የበዛ ትኩረትን ትስባለች።

እንደ ተባበሩት መንግስታት አዲስ መረጃ ከሆነ የዕድገትና ትራንፎርሜሽን ዕቅድ በአገሪቱ መተግበር ከጀመረ ወዲህ በከተማዋ መንግሥት ሲተገበራቸው በነበሩት ከፍተኛ መዋዕለ-ንዋይ የሚጠይቁ የመንገድ፣ የቤቶች፣ የባቡር፣የኢንዱስትሪ ማዕከላት፣ የቴሌኮም ማስፋፊያዎች፣ የኤርፖርት ማስፋፊያዎች፣ የትምህርትና የጤና ተቋማት በግሉ ዘርፍና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ተሳትፎ ጭምር የከተማዋ ጥቅል ዓመታዊ ምርት (GDP) ከ2000 – 2008 ድረስ በየአመቱ ከ15 በመቶ በላይ ሲያድግ ሲያድግ በአለም ፈጣኑ የሚባለው የሀገሪቱ ዕድገት ግን 10 በመቶ ነበር፡፡ ይህም በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ ከተሞች ባጠቃላይ ከሚፈጥሯቸው የሥራ ዕድሎች ውስጥ 68 በመቶው አዲስ አበባ ውስጥ እንዲሆን አድርጓል፡፡ ይህም ወጣቶች ከተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞችና የገጠር አካባቢ ጭምር ሥራ ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ እንዲጎርፉ ምክንያት ሆኗል፡፡

ይህ ሁኔታ ኢሕአዴግእመራበታለሁ ከሚለው ያልተማከለ አስተዳደርና የፌደራላዊ አደረጃጀት አንፃር በሂደት እየተቀየረ የሚሄድ ነው ተብሎ ሲጠበቅ የነበረ ቢሆንም አሁንም ድረስ ችግሩ ጭራሽ እየተባባሰ በመሄድ መንግሥት ሲከተል የነበረው የልማት ስትራቴጂ ከናካቴው ችግሩን የሚያባብስና አዲስ አበባ ከሌሎች የሀገሪቱ ከተሞች ጋር ያላትን ልዩነት የሚያሰፋ መሆኑ በግልጽ እየታየ ነው።ከዚህ በተጨማሪም የአገሪቱ አደረጃጀት/የክልሎች አወቃቀር ቋንቋና የዘውግ ማንነትን ማዕከል አድርጎ የተመሰረተ በመሆኑ በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ የሌላ ክልል ባለኃብቶችና ተወላጅ ኢትዮጵያውያን እንደመጤ ▶ የሚታዩበት የፖለቲካ ሥርዓት ከአዲስ አበባ ውጪ ኃብትን ሥራ ላይ ማዋል ከፍተኛ አደጋ የሚያስከትል ውሳኔ እያደረገው ይገኛል።በዚህም ምክንያት በርካቶች ከክልሎቻቸው ውጪሲሠሩ የሚያጋጥማቸው የደህንንት ስጋት ስላልተቀረፈ ኃብትና ንብረታቸውን ወደ አዲስ አበባ ማዞርን ይመርጣሉ። ይህ ደግሞ ክልሎች የንግድና ኢንቬስትምንት ማዕከል እንዳይሆኑ እያደረጋቸው በመሆኑ በክልል የሚኖሩ ወጣቶች በተለይም የዩንቨርሲቲ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ በአቅራቢያቸው ሥራ ማግኘት አዳጋች እየሆነባቸው መጥቷል።በመሆኑ፣ ለሥራ ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ በስፋት እንዲመጡ ይገደዳሉ።

ይህ ለክልል ከተሞች ዕድገት ማነቆ ከመሆኑም ባሻገር አዲስ አበባን ከፍተኛ ጫና ውስጥ እየከተታት ይገኛል። በከተማዋ የሚስተዋለው ስር የሰደደ ድህነት፣ የከፋ የኑሮ ውድነት፣ እየተበራከተ የመጣ ወንጀል፣ ከኅብረተሰብ ባህልና ሞራል ያፈነገጡ ድርጊቶች መበራከት፣ ለትንበያ እንኳን የሚያስቸግር የቤትና የቦታ የኪራይም ሆነ የሽያጭ ዋጋ፣ ቅጥ ያጣ የሕዝብ ትራንስፖርት ችግርና በአጠቃላይ የከተማው የኑሮ አመቺነት እየቀነሰ መምጣት ዋነኛ ምክንያት ከሌላ ከተማ እንደዚሁም ከገጠር የሚመጣው ከፍተኛ የሕዝብ ፍልሰትከከተማዋ የማስተናገድ አቅም በላይ ስለሆነ ነው።

ባጠቃላይ አዲስ አበባ አንድ ልጅ ያላቸው ወላጆችአፈር አይንካሽ ብለው ልጅንእንደሚያሳድጓት ልጅ ሙሉ ትኩረት ተሰጥቷት፤ ሌሎች ከተሞች ደግሞ ትኩረት ተነፍጓቸው በመቆየታቸው ከተማዋ በፍጥነት አድጋለች፤ ከሌሎች ከተሞች ጋር ያላት ልዩነትም የሰማይና የምድር ያህል የሰፋ ነው። በመሆኑም የሁሉንም ቀልብ የምትስብ አውራ ከተማ ሆናለች። ሌሎች ተመልካች ያጡ ነገር ግን ትልቅ አቅም ያላቸው ከተሞች የሚገባቸውን ያህል ትክረት አግኝተው የመሰረተ ልማት ግንባታ ካልተስፋፋባቸው፣እንደዚሁም ዜጎች በሰላምና ደህንነቱ በተጠበቅ አካባቢ የመኖር መብትና ዋስትናቸው እስካልተከበረ ድረስ ከክልል ከተሞችና ከገጠር ወደ አዲስ አበባ የሚደረገው ፈር ያልያዘ ፍልሰት አይቆምም፤ መዘዙም ብዙ ነው።

የኀች ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ የመሥራት ሕገመንግሥታዊ መብት ነው፤ ነገር ግን ወደ አንድ ከተማ የሚደረግ ያለቅጥ የበዛ ፍልሰት የከተማውን ባሕል፣ የአኗኗር ዘይቤና ከተሜያዊ ማንነት፣ እንደዚሁም የኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ሽሚያ ነባሩ ሕዝብ ላይ የሚያስከትለው ችግር ውሎ አድሮ የፖለቲካና የደህንነት ችግር እስከመሆን መድረሱ አይቀርም።

ስለሆነም ዜጎች ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው የመኖር፣ የመሥራትና ኃብት የማፍራት መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በአንድ ቦታ ተርጋግቶ ለሚኖሩበት ማኅበረሰብና አካባቢ ሁለንተናዊ ዕድገት አስተዋፆ እያደረጉ እንዲኖሩ የፖለቲካ፣ የሕግ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ጉዳዮች ክፍተቶችን ማስተካከል ለነገ የሚባል ሥራ አይደለም። በሀገሪቱ የተመጣጠነ የከተሞች እድገትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገው የፖሊሲ ማዕቀፍ ተነድፎ፣ ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉ የክልል ከተሞች የንግድ፣ የቱሪዝም፣ የኢንቬስትመንት፣ የመዝናኛ፣ የስፖርትና አጠቃላይ የሥራ ፈጠራ ማዕከል ካልተደረጉ አዲስ አበባ ላይ የሚቀርበው የባለቤትነት ውዝግብ መቼም ቢሆን ጋብ አይልም።

የክልል ከተሞች አዲስ አበባን በሚገዳደር ደረጃ መሰረተልማት ▶



▶ ከተስፋፋባቸው፤ ለመኖርያም ለመሥሪያም የሚያመቹና ደህንነታቸው የተጠበቀ ከሆነ ትልቅ የገብያ ማዕከል ይሆናሉ። ዜጎችም በአቅራቢያቸው ሥራ ስለሚያገኙ የሕዝብ አኗኗር የተርጋጋ ይሆናል። ፍልሰትን ሙሉ ለሙሉ ማስቆም ባይቻልም፤ መቆጣጠርና መተንበይ ስለሚቻል በልማት እቅዶች ላይ ተገቢውን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከግምት ውስጥ እያስገቡ አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ይቻላል።

አዳማ፣ ነቀምት፣ ጂማ፣ ደንቢዶሎ፣ ጭሮ፣ አምቦ፣ ቡሌ ሆራ፣ፍቼና ሌሎችም በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ከተሞች በፍጠነት ሲያድጉና የልማት ማዕከል ሲሆኑ አዲስ አበባ ላይ የተቸከለው የኦሮሞ ፖለቲካ አዲስ ቅርጽ እየያዘ መሄዱ አይቀርም። በተጨማሪም ባህር ዳር፣ ደብረ ብርሃን፣ ጎንደር፣ ወልዲያ፣ ደብረ ማርቆስና ፍኖተ ሰላምና ሌሎችም በአማራ ክልል የሚገኙ ከተሞች ከአዲስ አበባ ጋር ተነፃፃሪ በሆነ ደረጃ ሲያድጉና ሲለሙ ከክልሉ ወደ አዲስ አበባ የሚደረገው ፍልሰት ይቀንሳል። በተመሳሳይ በሌሎች ክልሎች የሚገኙ ከተሞች በዘመናዊ ማስተር ፕላን እየተመሩ የሚያድጉበትና የልማት ማዕከል የሚሆኑበትሥርዓት ከተበጀላቸው፣ ቀየውን ጥሎ ወደ አዲስ አበባ የሚኮበልለው ወጣት ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል፤ በተቃራኒው ፍልሰቱ ከአዲስ አበባ ወደነዚህ ከተሞች መሆን ይጀምራል።

## ከጭቅጭቁ መውጫ መፍትሄ

እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ በርካታ የዓለማችን ሀገሮች በጣም ትልቅ ዋና ከተማና የኮሰመኑ ሌሎች ከተሞች ያላቸው አገሮች አሉ። እነዚህ ሀገሮች የዋና ከተሞቻቸው ዕድገታቸው ሄዶ ሄዶ የደረሰበትን መጨናነቅ ለማስተንፈስ አማራጭ ከተሞችን ከመገንባት ዋና ከተማ እስከመቀየር የደረሱ አሉ።ምዕራብ አፍሪካዊቷ ናይጄሪያ ዋና ከተማዋን ከሌጎስ ወደ አቡጃ፣ ታንዛኒያ ከዳሬሰላም ወደ ዶዶማ፣ ኮትዲቯር ከአቢጃን ወደ ያማሶኩሩ መዲናቸውን አዙረዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ ሁለተኛና ሶስተኛ ዋና ከተማ እስከመገንባት የደረሱ አሉ፤ ለዚህም ሰሜን አፍሪካዊቷ ግብጽ የካይሮ ከተማ ከልክ በላይ በመስፋቷና የሕዝብ ብዛቷ ከሃያ ሚሊዮን በመብለጡ ሌላ አዲስ ዋና ከተማ ኒው ካይሮ ብላ ግንባታ እንድትጀምር አስገድዷታል።የናይጄሪያ ጎረቤት ቤኒኒም ዋና ከተማ የምትባለው ፖርት-ኖቮ ብትሆንም ትልቋ ከተማና የመንግሥት መቀመጫዋ ኮቶኑ ናት።በአፓርታይድ ሥርዓት የነበረውን መድሎ በአዲስ አስተሳሰብ ለመቀየር ደቡብ አፍሪካም በተለየ አካሄድና የተለየ የፖለቲካ ታሪካቸውን ለማቻቻል ሶስት ዋና ከተማ እንዲኖራት ተደርጓል፤ የመንግሥት ሥራ አስፈፃሚዎች የሚገኙባት ዋና ከተማ ፕሪቶሪያ ስትሆን፤ ፓርላማው ደግሞ ኬፕ ታውን ከትሟል፤ የሀገሪቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ ብሎም ፎንቴይን በምትባለው ከተማ ይገኛል።

ወደ አሜሪካ ያቀናን እደሆነ ዋሺንግተን ዲሲ የፌደራል መንግሥቱ መቀመጫ ብትሆንም ከተማዋ በጣም ትንሽና ከ700 መቶ ሺህ በላይ ሕዝብ የማይኖርባት አነስተኛ ከተማ ናት፤ ይህም ከቂርቆስና ቦሌ ክፍለ ከተሞች የህዝብ ብዛት አይበልጥም ማለት ነው። ነገር ግን አሜሪካ የፋይናንስና ዲፕሎማሲውን በኒውዮርክ፤ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂውን ሳን ፍራንሲስኮና አካባቢው ባሉ የካሊፎርኒያ ከተሞች፤ መዝናኛውን ሎስ አንጀለስ፤ የነዳጅ ኢንዱስትሪውን ቴክሳስ፤ ዩንቨርሲቲዎቹን በሁሉም ከተሞች በማስፋፋት ያልተማከለና የተመጣጠነ የከተሞች ስርጭትና ዕድገት እንዲኖር አድርገዋል። በዋና ከተማቸው ላይ የሚኖርን አላስፈላጊ ጫና አስወግደዋል፡፡ ሀገራችን በርካታ ከተሞች ያስፈልጓታል። ለዚህም አዲስ አበባን የሙጥኝ በማለት ሌሎች ከተሞች በትንሽ ኃብትን ሊበለጽጉበት የሚችልን ውስን ኃብት ማባከን ተገቢ ነው ተብሎ አይታመንም። ስለሆነም ለተመጣጠነ የከተሞች ዕድገት ትልቅ ትኩረት በመስጠትና ተገቢውን ኃበት በመመደብ፤ እንደዚሁም ብቃት ያላቸው አመራሮችን ለኃላፊነት በማብቃት ከተሞች በወጉ እንዲለሙ ያደርጋል። በዚህም አዳማ፣ ባህር ዳር፣ ድሬ ዳዋ፣ ጎንደር፣ መቀሌ፣ ሐዋሳ፣ አርባ ምንጭ፣ ደብረ ብርሃን፣ ጂማ፣ ነቀምት፣ ጂግጂጋና ሰመራ ቢያንስ አንድ ሚሊዮን ሕዝብ ማስተናገድ የሚችሉበትን አቅም በአስር ዓመት ውስጥ መፈጠር አለበት።

ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የተቀናጀ የከተሞች ልማት ፈንድ በማቋቋም ከፌደራል መንግሥትና ከተሞቹ ከሚገኙባቸው የክልል መንግሥታትና የልማት አጋሮች እንደዚሁም ከመላው የከተሞቹ ነዋሪዎች ኃብት በማሰባሰብ ከተሞቹን የኢንዱስትሪ፣ የቱሪዝምና የንግድ ማዕከል የማድረግ ሥራ መሠራት ይባዋል።አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከባለድርሻዎች ጋር በመምከርና ጉዳዩን ዝርዝር ጥናት እየሠሩ ከአዲስ አበባና ድሬ ዳዋ ተጨማሪ የፌደራል ከተሞች እንዲኖሩና የዋና ከተማዋን ጫና እንዲጋሩ ይደርጋል።

## ሁለትና ከዚያ በላይ ዋና ከተሞች ያላቸው አገሮች

| ቁጥር | አገር | ዋና ከተሞች |
|---|---|---|
| 1 | ቤኒን | ኮቶኑና ፖርቶ-ኖቮ |
| 2 | ቦሊቪያ | ላ ፓዘ ና ሱክሬ |
| 3 | ቺሌ | ሳንቲያጎና ቫልፓራይሶ |
| 4 | ጆርጂያ | ኩታይሲ ና ተቢሊሲ |
| 5 | ሆንዱራስ | ኮማጉዌላ ና ቴጉሲጋለፓ |
| 6 | አይቮሪ ኮስት/ | ኮት ዲቯር አቢጃን ና ሙሶኩሮ |
| 7 | | ማሌዢያ |
| 8 | ሞንቴ ኔግሮ | ሴቲኚና ፖድጎሪካ |
| 9 | ኔዘርላንድሰ | አምስተርዳምና ዘ ሄግ |
| 10 | ደቡብ አፍሪካ | ብሎመ ፎንቴይን፣ ኬፕ ታውንና ፕሪቶሪያ |
| 11 | ደቡብ ኮሪያ | ሴጆንግና ሴኡል |
| 12 | ስሪላንካ | ኮሎምቦና ኮቴ |
| 13 | ስዋዚላንድ | ሎባምባና ምባባቤ |
| 14 | ታንዛኒያ | ዳሬሰላም ና ዶዶማ |
| 15 | ምዕራብ ሳሓራዊ | ላዩኔና ቲፋሪቲ |

ምንጭ፡- worldatlas.com

* የዜጎች መድረክ የኢዜማን አቋሞች ከማስረዳት በተጨማሪ የኢዜማ አባላት እና ደጋፊዎች እንዲሁም ኢትዮጵያዊያ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ምክንያታዊ ውይይቶች የሚያደርጉበት መድረክ ነው፡፡ በዚህ ጽሑፍ የተጠቀሱት ሀሳቦች የጸሐፊው ሲሆኑ፣ ኢዜማ በአዲስ አበባ እና በአጠቃላይ የከተሞች ልማትን በተመለከተ ዘርፍዘለል የፖሊሲ ሰነድ በቅርቡ ይፋ ያደርጋል፡፡

# ‹‹ሕገ መንግሥቱ ካለው ፋይዳ በተጨማሪ እንደ አንድ አገራዊ መግባቢያ ማዕከል እንዲሆን ማሻሻያው ላይ መስራት ይገባል››

## የሺዋስ አሰፋ የኢዜማ ሊቀመንበር

ነሐሴ 24 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት የተቀረፀበትና የፀደቀበት ሂደት እንዲሁም ወደ ፊት ሊኖረው የሚገባ የተፈጻሚነት ሁኔታ ላይ ውይይት በማካሄድ፣አብዛኛው ዜጋ የሚስማማበት መንገድ መፍጠር ለአገራዊ መግባባት ወሳኝ ድርሻ ስለሚጫወት በሕገ መንግሥቱ ዙሪያ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ሊቀ መንበር የሺዋስ አሰፋ ገለፁ፡፡

ነሐሴ 16 ቀን 2012 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በብሔራዊ መግባባት ዙሪያ በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን (ECA)አዳራሽ ባዘጋጀው ውይይት ላይ «ሕገመንግሥት እና ሕገመንግሥታዊነት ለብሔራዊ መግባባት»በሚል ርዕስ ያዘጋጁትን ጽሑፋቸውን ያቀረቡት የኢዜማ ሊቀ መንበር የሺዋስ አሰፋ፣ ሕገ መንግሥት ለሀገራዊ መግባባት ድርሻ ስለሚጫወት በሕገመንግሥቱ ዙሪያ ውይይት ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን በጽሑፋቸው አስረድተዋል፡፡ የብሔራዊ መግባባትን አስፈላጊነት «ሀገራዊ መግባባት ላይ መድረስ ካልቻልን ለልጅ ልጆቻችን የተሻለች ኢትዮጵያን ማውረስ ይቅርና የነበረውንም ሁኔታ ማስቀጠል የምንችል አይመስለኝም»በማለት አስረድተዋል፡፡ ብሔራዊ መግባባት ላይ መድረስ ካልተቻለ ከትናንት የተሻገረ፣ የተደራረበ እና የተወሳሰበ ችግር ለትውልድ እናስተላልፋለን ሲሉ ማሳሰቢያ ሰጥተዋል፡፡ብሔራዊ/ሀገራዊ መግባባት በአንድ ጊዜ የሚጠናቀቅ አይደለም ያሉት አቶ የሺዋስ አሰፋ፣የነገ ሀገራዊ መግባባት እና ሰላም የዛሬ ሀገራዊ ውይይት ውጤት ነው በማለት ብሔራዊ መግባባትን ለማምጣት ውይይት አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በሕገመንግሥቱ ዙሪያ መግባባት ላይ ለመድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ሀሳቦች ሊስተናገዱበት እንደሚገባ፣ የማርቀቅ ሂደቱም አሳታፊ መሆን እንዳለበት ሊቀመንበሩ ገልፀዋል፡፡ሕዝብ፣ሕገመንግሥቱን በሙሉ ልብ እንዲቀበለው ከተፈለገም በሂደቱ ተሳታፊ ሊሆን እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡ ሕዝብ ያልተሳተፈበትን እና ያልመከረበትን ሰነድ የሀገር የበላይ ሕግ አድርጎ ለመውሰድ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል ብለዋል፡፡

ሕገ መንግሥት ዘላለማዊ ሰነድ አይደለም ያሉት ሊቀመንበሩ፣ ማንኛውም ሕግ በሚረቀቅበት ወቅት ያለውን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ እንደሚረቀቅ አስታውሰው፣ሕጎች በየጊዜው ሊገመገሙ እና መሻሻል ያለባቸውም ሊሻሻሉ እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡ሕገ መንግሥቱም ከዚህ የተለየ ስላልሆነ ማኅበረሰቡ የሚደርስበት የአኗኗር፣የአስተሳሰብ፣የባህል እንዲሁም የማንነት ደረጃ በየግዜው ሊቀያየር እንደሚችል ታሳቢ በማድረግ ሕገመንግሥቱን ማሻሻል እንደሚያስፈልግ በጽሑፋቸው አስረድተዋል፡፡ ሕገመንግሥቱን እንደ ፈጣሪ ቃል የማይቀየር እና እንከን የለሽ አድርጎ ማሰብና አይነኬ ማስመስል ፍፁም ስሕተት ነው በማለት ሕገመንግሥቱ እንደማይነካ ሰነድ ተደርጎ መቆጠር እንደሌለበት ጠቁመዋል፡፡

የሕገመንግሥትን ዓላማ በጽሑፋቸው የዳሰሱት የሺዋስ አሰፋ፣የሕገ መንግሥት ዋነኛ ዓላማ የመንግሥትን ሥልጣን መገደብ እና እኩልነት ማስፈን መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ በሕገመንግሥት ውስጥ መንግሥት፣የዜጎቹን መብት ሊያፍንበት የሚያስችሉ የሕገመንግሥት አንቀፆች እንዳይኖሩ መጠንቀቅም ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ ሕገመንግሥት፣ዜጎች እንደ ግለሰብ መብታቸውን የሚጠይቁበት መሆን እንዳለበት በጽሑፋቸው ያነሱት ሊቀመንበሩ፣ሕገመንግሥት በቡድን ካልመጣህ አላውቅህም የሚል ሰነድ መሆን የለበትም ብለዋል፡፡የግለሰብን መብት ሙሉ በሙሉ የማያከብርና የማያስከብር ሕገ መንግሥት ዋና ዓላማውን የሳተ ይሆናል በማለት አንድ ሕገመንግሥት ዜጎችን በግለሰብ ደረጃ እውቅና የሚሰጥ፣ መብታቸውንም የሚያስከብር ሰነድ መሆን እንዳለበት ገልፀዋል፡፡ ይህ ማለት ግን ለቡድን መብቶች እውቅና አይስጥ ማለት አይደለም ብለዋል፡፡ሰነዱ ለግለሰብም ሆነ ለቡድን መብቶች እውቅና የሚሰጥ መሆን እንዳለበት እና ሁለቱንም እኩል የሚያስከብር ሰነድ መሆን እንዳለበት በጽሑፋቸው አስረድተዋል፡፡

በሕገመንግሥት ሁሉም ድንጋጌዎች ሁሉም ዜጋ ይስማማል ብሎ ማሰብ አይቻልም ያሉት የሺዋስ፣ አብዛኛውን ዜጋ ለማስማማት መፍትሔ ይሆናሉ ያሉትን ሀሳብ በጽሑፋቸው አንስተዋል፡፡የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩር ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አንስተዋል፡፡ሕገ መንግሥት በእያንዳንዱ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሰነድ ሊሆን አይችልም ያሉት ሊቀመንበሩ፣ዋናው ምክንያትም በሁሉም ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ስምምነት ላይ መድረስ ስለማይቻል ነው ብለዋል፡፡ለሕዝብ ውይይት የሚቀርቡ ጉዳዮች በበዙ ቁጥር ልዩነቶችም እየሰፉ የሚሄዱበት ዕድል ስለሚያሰፋ ሕገ መንግሥት በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ እንዲያተኩር በማድረግ ልዩነቶችን ማጥበብ ይቻላል በማለት መፍትሔ ያሉትን ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡

ሕገ መንግሥት በትክክለኛው ሥነ ሥርዓት መረቀቁን፣የሕዝብይ ሁንታ ማግኘቱን እና በዴሞክራሲያዊ መንገድ መፅደቁን ማረጋገጥ ከተቻለ ሕገ መንግሥትን የሚቃወሙት ዜጎች ቁጥር አነስተኛ ማድረግ እንደሚቻል በጽሑፋቸው የጠቆሙት የሺዋስ አሰፋ፣ሕገ መንግሥቱ ካለው ፋይዳ በተጨማሪ እንደ አንድ ሀገራዊ መግባቢያ ማዕከል እንዲሆን ማሻሻያው ላይ ፍጹም አሳታፊነት በተሞላበት ሁኔታ መስራት እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡ ማሻሻያው ላይ ለመሥራት ለሁሉም ፖለቲካ ፓርቲዎች ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡





# «በሁለትዮሽ የጋራ መድረኩ ላይ ትልቅ ተስፋ አለን»

## ዋሲሁን ተስፋዬ - የኢዜማ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ

ነሐሴ 24 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ በሌሎች ክልሎች የሁለትዮሽ መድረክ ማቋቋም ከኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ባገኘነው መረጃ መሠረት በዜጎች መድረክ ቁጥር 51 ላይ መዘገባችን ይታወሳል፡፡ ከዘገባው በኋላ የሁለትዮሽ የጋራ ምክር ቤት በሌሎችም ክልሎች እንዲቋቋም ጥሪ እንደተረገላቸው የኢዜማ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ገልጸዋል፡፡

በየጊዜው የሚደርሱ የመብት ጥሰቶች እና ከእስር ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ ችግሮች ሲኖሩ የጋራ መድረኩ በፍጥነት እየተወያየ ችግሮችን እንዲፈታ፣ የተሻለ አቅጣጫ በመያዝ ሥራውን እንደሚጀመር በኦሮሚያ፣ በአማራ በደቡብ እና በሲዳማ ክልሎች ላይ የሁለትዮሽ የጋራ ምክር ቤት የሚሳተፉ የብልፅግና የሚወከሉ አመራሮችን ለኢዜማ ማሳወቃቸውን ኢዜማም ጥሪውን በመቀበል በየክልሉ ያሉ የዞን አስተባባሪዎች እና በምርጫ ወረዳ ላይ ያሉ አመራሮችን በሚቋቋመው ምክር ቤቱ እንዲሳተፉ መምረጡን፣በሚቀጥለው ሳምንት የሁለትዮሽ የጋራ ምክር ቤት ተቋቁሞ ሥራ ይጀምራል ተብሎ እንዲመጠበቅ ከድርጅት ጉዳይ ያገኘነው መረጃ ያሳያል፡፡

«በንግግር የማይፈታ ነገር የለም፡፡እስካሁን ድረስ የሚፈጠሩ ችግሮችን የምንፈታበት መንገድ የለም ነበር፡፡ ይሄ መድረክ እስካ ለድረስ ችግሮቻችን እዚህ ላይ በማቅረብ እንፈታለን ብለን እናምናለን፡፡ በሁለትዮሽ የጋራ መድረኩ ላይ ትልቅ ተስፋ አለን።»በማለት የድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ተናግረዋል ፡፡

# «በዴሞክራሲያዊ መንገድ የእኛን ሃሳብ ወስደው እንዲሸጡልን እንፈልጋለን፡፡»

## ወንድወሠን ተሾመ - የሙያ ማኅበራት ተጠሪ

ነሐሴ 24 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በሐምሌ ወር ላይ በተጓደሉ የብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ አባላት ምትክ አዳዲስ ሹመቶችን መስጠቱ ይታወሳል። አዳዲሶቹ የብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ አባላት በተሰጣቸው የሥራ ዝርዝር አማካኝነት ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡ ከአዳዲሶቹ የብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት መካከል የሆኑት የሙያ ማኅበራት ተጠሪ ወንድወሠን ተሾመ ያለፈውን አንድ ዓመት አጠቃላይ የሥራ ሪፖርት በማስገባት ለቀጣይ ዓመት የሚሠሩ አዳዲስ እቅዶችን በማውጣት ለሥራ እየተዘጋጁ መሆናቸውን አሳውቀዋል፡፡

የሙያ ማኅበራት ኮሚቴውን ማጠናከር አስፈላጊ በመሆኑ በኮሚቴው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ዘጠኝ የቋሚ ኮሚቴ አባላት ለመምረጥ በሂደት ላይ የሚገኙ ሲሆን ከዘጠኙ ውስጥ ስድስት አባላት በመምረጥ ሥራቸውን ለመጀመር በዝግጅት ላይ ናቸው። በሂደት ለቦታው ተመጣጣኝ የሆነ ሰው በመፈለግ እንደሚያካትቱ ተገልጿል፡፡ በኢዜማ በኩል በግል መሥሪያ ቤት የተቀጠሩ ሰዎች ትኩረት ተደርጎባቸው እንደሚሠራ ወንድወሰን ገልፀዋል። በአዲስ አበባ ውስጥ ከ1500 በላይ ትምህርት ቤቶች እንዳሉ እና 60 በመቶ የሚሆኑት የአዲስ አበባ መምህራን በግል ትምህርት ቤቶች እንደሚያስተምሩ የጠቀሱት ተጠሪው፣ መምህራኖቹ በሙያ ማኅበራት አለመደራጀታቸውን አስታወሰዋል።

በኢትዮጵያ ከኢዜማ በፊት አንድም የፖለቲካ ፓርቲ የሙያ ማኅበራትን ለማደደራጀት ትኩረት ሰጥቶ በብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ደረጃ ያሳተፈ አለመኖሩን እና ከዚህ በፊት የነበሩት ብዙዎቹ የሙያ ማኅበራት በመንግሥት ተፅዕኖ ስር ታጥረው የመንግሥት አገልጋይ ሆነው የካድሬ ሥራ ሲሰሩ በመቆየታቸው ወንደወሠን ጨምረው አስታውሰዋል። ይህን ችግር በመረዳት ኢዜማ ሁለት የሙያ ማኅበራት ተጠሪዎችን በብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረጉን ገልጸዋል፡፡

«የሙያ ማኅበራት የእኛ አገልጋይ ይሁኑ ብለን አይደለም የምናስበው፤በዴሞክራሲያዊ መንገድ የእኛን ሃሳብ ወስደው እንዲሸጡልን እንፈልጋለን፡፡ እነሱን በእኛ እጅ ውስጥ የማስገባት ዓላማ የለንም፡፡ የሙያ ማኅበራትን መብት አስጠባቂ ብቻ አድርጎ የመቁጠር ባህል አለ፡፡ የኢዜማ የሙያ ማኅበራት ተጠሪዎች ግን ግዴታውን ለሚወጣ ሠራተኛ ነው ድጋፍ የሚያደርጉት።» ብለዋል፡፡

የሙያ ማኅበራት ለምን እንደተደራጁ የግንዛቤ እጥረት እንዳለ ያነሱት የኢዜማ የሙያ ማኅበራት ተጠሪ«የሙያ ማኅበራት የመንግሥት ጉዳይ አስፈጻሚ እንደነበሩ ሠራተኛው ደጋግሞ ስላየው በነጻነት መደራጀት መብት ነው ብሎ ያለማሰብ እና መደራጀት ማለት በቀጥታ የመንግሥትን ሥራ ማስፈጸም ነው ብሎ ማሰብ ከዚህ በፊት የተደራጁም ያልተደራጁም ሰዎች እሳቤ ስለሆነ ይሄን መስበር ትልቅ ፈተና ነው።» ብለዋል።ከሁሉም በላይ የመደራጀት ፍላጎት ማጣት፣ ሠራተኛው መብትን መጠየቅ እንጂ ግዴታውን መወጣት አለመፈለጉ ትልቅ ተግዳሮት እንደሆነባቸው ተጠሪው ገልጸዋል፡፡





# «ከመሬት ወረራ እና የቤቶች ዕደላ ጋር ሁሉም እውነት እንዳይገለፅ የሚፈልግ አካል ያለ ይመስላል»

## ናትናኤል ፈለቀ የኢዜማ ሕዝብግንኙነት ኃላፊ

## «ኢዜማ መግለጫውን መስጠት ያልቻለው ከ4 ሰው በላይ ስብሰባ ለማካሄድ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ፍቃድ መጠየቅን ስለሚያዝና ኢዜማም ያንን ፍቃድ ይዞ ስላልቀረበ ነው።» - ፖሊስ

ነሐሴ 24 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በአዲስ አበባ ከተማ መሬት ወረራን እና የጋራ መኖሪያ ቤቶች ኢፍትሃዊ ዕደላን በተመለከተ ያካሄደውን ጥናት ሰኞ ነሐሴ 25 ቀን 2012 ዓ.ም 8 ሰዓት (ከሰዓት)ለሕዝብ ይፋ እንደሚያደርግ አስታወቀ፡፡

ኢዜማ፣አርብ ነሐሴ 22 ቀን 2012 ዓ.ም ጥናቱን ይፋ ለማድረግ በራስ ሆቴል ጠርቶት የነበረው ጋዜጣዊ መግለጫ በፖሊስ ክልከላ ምክንያት ሳይካሄድ መቅረቱ የሚታወስ ነው፡፡ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ አባል የሆኑ ፖሊሶች በስፍራው ለነበሩ የኢዜማ አመራሮች«ጋዜጣዊ መግለጫው እንዲካሄድ ትዕዛዝ አልተሰጠንም»በሚል ጋዜጣዊ መግለጫውን ማካሄድ እንደማይችሉ የገለፁ ሲሆን፣በሥፍራው የነበሩት የኢዜማ አመራሮች በበኩላቸው ስለመግለጫው ለኢፌዴሪ ሰላም ሚኒስቴር በደብዳቤ ማሳወቃቸውን ለፖሊስ አባላቱ በመግለፅ ወደ ሰላም ሚኒስቴር በመደወልም የተፈጠረውን ለሚንስቴር መስሪያ ቤቱ አሳውቀዋል፡፡የፖሊስ አባላቱም ከኢፌዴሪ ሰላም ሚኒስቴር ጋርም በስልክ እንዲገናኙ አድርገዋል፡፡

የፖሊስ አባላቱ በስልክ ከሰላም ሚኒስቴር ጋር ከተወያዩ በኋላ«የሰላም ሚኒስቴር ሊፈቅድ የሚችለው ስብሰባዎችን እንጂ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን አይደለም።የመግለጫ ጉዳይ የሚመለከተው ፖሊስን ነው።»በማለት ጋዜጣዊ መግለጫውን ማካሄድ እንደማይቻል በሥፍራው ለነበሩ ለኢዜማ አመራሮች ገልፀዋል፡፡ በዚህ የተነሳም አርብ ነሐሴ 22 ቀን 2012 ዓ.ም በራስ ሆቴል ሊካሄድ ታስቦ የነበረው መግለጫም ሳይሰጥ ቀርቷል፡፡

ፖሊስ፣ ኢዜማ መግለጫውን እንዳይሰጥ ያስቆምኩት ከ4 ሰው በላይ ስብሰባ ለማካሄድ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ፍቃድ መጠየቅን ስለሚያዝ እና ኢዜማም ያንን ፍቃድ ይዞ ስላልቀረበ ነው ሲል ለአዲስ ሚድያ ኔትዎርክ ገልጿል፡፡ ዜጎች መድረክ ይህንን የፖሊስ አስተያየት ተከትሎ በጉዳዩ ላይ ሀሳባቸውን እንዲያካፍሉ የኢዜማ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ናትናኤል ፈለቀን አነጋግራለች፡፡ ኃላፊው በአስቸኳይጊ ዜአዋጅ ውስጥ ከ4 ሰው በላይ ሰው ሲሰበሰብ የመፍቀድ ሥልጣን ያለው ሰላም ሚኒስቴር ነው ብለዋል፡፡ ከዚህ ቀደም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከታወጀ በኋላ ሁለት ጊዜ ለሰጧቸው ጋዜጣዊ መግለጫዎች ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ በደብዳቤ አሳውቀውት ምንም ችግር ሳያጋጥማቸው መግለጫዎች መስጠታቸውን አስታውሰዋል፡፡ በተመሳሳይ ቦታ (በራስ ሆቴል) ኢዜማ ይዞት ከነበረው አዳራሽ አንድ ፎቅ ከፍ ብሎ ሌላ ስብሰባ ሲካሄድ እንደ ነበር የገለፁት ናትናኤል፣ፖሊስ ሲካሄድ የነበረውን ስብሰባ ፈቃድ እንዳለው እና እንደሌለው ለማጣራት አለመፈለጉን ገልፀዋል፡፡

አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከተደነገገ በኋላ ኢዜማ በሰጣቸው ጋዜጣዊ መግለጫዎች ፖሊስ ፍቃድ አላችሁ ብሎ ጠይቆ ያውቃል ወይ? በሚል ዜጎች መድረክ ላነሳችላቸው ጥያቄ ሰብሳቢው ሲመልሱ፣ፖሊስ ከዚህ ቀደም እንዲህ ዓይነት ጥያቄ አቅርቦላቸው እ ን ደ ማ ያ ው ቅ ገልፀው፣ከመሬት ወረራ እና የቤቶች ዕደላ ጋር ሁሉም እውነት እንዳይገለፅ የሚፈልግ አካል ያለ ይመስላል ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ መሬት ወረራን እና የጋራ መኖሪያ ቤቶች ኢፍትሃዊ ዕደላ ላይ የተደረገውን ጥናት ውጤት ሰኞነሐሴ 25 ቀን 2012 ዓ.ምበጋዜጣዊ መግለጫ ይፋ እንደሚደረግ እና ይህንኑም እንዲያውቁት በሚል አርብ ነሐሴ 22 ቀን 2012 ዓ.ም ለሰላም ሚኒስቴር እና ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ደብዳቤ መላኩን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ለዜጎች መድረክ ገልፀዋል።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ከሕዝብ የደረሱትን በርካታ ጥቆማዎች በመነሻነት በመያዝ በአዲስ አበባ ከተማ እየታየ ያለውን የመሬት ወረራ ከብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የተውጣጣ ኮሚቴ በማዋቀር ላለፉት ሁለት ወራት የማጣራት ሥራ ሲያካሄድ እንደነበረ ይታወሳል። ኢዜማ በጥናቱ ያገኘውን ውጤት ይፋ ከማድረጉ በፊት የከተማ አስተዳደሩን ምላሽ ለማካተት ለከተማው አስተዳደር ከንቲባ ጽሕፈት ቤት እና በስሩ ለሚገኙት የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኤጀንሲ እና የአዲስ አበባ መሬት ልማት ቢሮ በደብዳቤ ጠይቆ የነበረ ቢሆንም አንዳቸውም ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል።

# ኢዜማ በሠገን አካባቢ በሚገኙ አባላቶቹ ላይ ከፍተኛ ጫና እየደረሰባቸው ነው አለ

ነሐሴ 24 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)ሠገን አካባቢ ምርጫ ወረዳ የሚገኙ አባሎች፣ የምረጫ ወረዳ አመራሮች እና ደጋፊዎች ላይ ከፍተኛ ጫና እየተደረገ ነው ሲሉ የኢዜማ የድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አባልና የደቡብ ክልል ቀጠና አስተባባሪ አዲስ ለማ አሳወቁ።

በሠገን የሚገኙ የኢዜማ መዋቅሮችን ለመገምገም፣ የአንድ ዓመት የሥራ አፈጻጸም ምልከታ ለማድረግ እና ተገቢውን የፖለቲካዊ ድጋፍ ለመሰጠት ወደ ቦታው ያቀኑት የደቡብ ክልል ቀጠና አስተባባሪ የተለያዩ የፓርቲ ሰነዶች (የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ የዲስፕሊን መመሪያ፣ የፋይናንስ መመሪያ፣ የምርጫ ቦርድ የእውቅና ሰርተፍኬት)ለአምስት ምርጫ ወረዳዎች እና ለአንድ ልዩ ምርጫ ወረዳ በአጠቃላይ ለስድስት ምርጫ ወረዳዎች አስረክበዋል፡፡

በሠገን የሚገኙ የኢዜማ አባላት በራሳቸው ጥረት ጠንካራ አደረጃጀት በመፍጠር የኢዜማን የፖለቲካ አመለካከት ለአባላቶች በማስተማር በወረዳ እና በክላስተር ደረጃ ጽሕፈት ቤት ከፍተዋል፡፡ ነገር ግን በአካባቢው በመንግሥት በኩል የኢዜማ አመራሮች፣ አባላት እናደጋፊ ናቸው ብለው ያሏቸው ላይ በሀሰት ክስ እያሳደዱ፣ በሕግ አግባብ እንዳይዳኙ እና በግል ሕይወታቸው ጭምር በመግባት ከሥራ እንዲሰናበቱ፣ ከሥራ መደብ ዝቅ እንዲሉ በማድረግ ከፍተኛ ጫና እያደረሱ እንደሆነ የደቡብ ክልል አስተባባዊው አሳውቀዋል። ከሥራቸው ማሰናበት እና ከደረጃ ዝቅ ማድረግ ያልቻሉትን በሰበብ አሳባቡ ደሞዝ እንዲቆረጥባቸው በማድረግ የሥነ ልቦና ተፅዕኖ እያደረጉባቸው እንደሚገኝ አዲስ ለማ ለዜጎች መድረክ ገልጸዋል፡፡

አባላትን ካሰሩ በኋላ «የሚደርስላችሁ የለም፡፡ እናንተ ተፎካካሪ ነን ብላችሁ ጊዚያችሁን ታጠፋላችሁ፣ ኢኮኖሚያችሁን ትጎዳላችሁ፣ መስዋዕትነት ትከፍላላችሁ፣ በእኛ ቁጥጥር ስር ስለሆናችሁ እንኳን ማሰርና ከሥራ ማሰናበት፣ ልንገላችሁም እንችላለን፡፡ ይሄ መብታችን ነው ስለ እናንተ የሚሟገት የለም፡፡»እያሉ እንደሚያስፈራሯቸውም አዲስ ወደ ቦታው ባቀኑበት ጊዜ አባላት ነግረዋቸዋል፡፡

አስተባባሪው በጋሞ ጎፋ ብር ብር ምርጫ ወረዳ የኢዜማን የኢዜማ አባልን የቀበሌው ታጣቂዎች ሰበብ ፈጥረው አስረው እንደ ደበደቡት አባሉም በድብደባ ብዛት መሞቱን በመግለጽ አባላት የሚደርስባቸው ተፅዕኖና ጫና ለኢዜማ ዋና ማዕከል ቢያሳውቁም ፈጣን ድጋፍ አለማግኘታቸው እና መረጃውም ለሕዝቡ እንዲደርስ አለመደረጉ ችግር እንደሆነባቸው አክለው ገልጸዋል፡፡